“አብዛኞቹ ችግሮቻችን ተለያይተን ቀርቶ በጋራ ብንረባረብባቸዉ እንኳን በቀላሉ ለመፍታትም ሆነ ለጊዜዉ ለመቅረፍ የሚያስቸግሩ ናቸዉ፡፡ ለአሁኑም ሆነ ለወደፊቱ የሚያዋጣን ከሚለያዩን ይልቅ በሚያቀራርቡን ላይ ማተኮር ስለሆነ ትብብሩ በዘረጋዉ የጋራ የትግል መድረክ በመተማመን ወደፊት እንጓዝ እላለሁ፡፡” *በስተን በተደረገዉ የትብብሩ ህዝባዊ ስብሰባ አቶ ሀሰን ሁሴን ከተናገሩት የተቀነጨበ፡፡ ሙሉዉ ንግግር እነኾ፡፡*

Akkam nagayaa? ጤና ይስጥልኝ፤ እንደምን ሰንብታችኋል፤

ከሰላምታዬ በማስከተል በአይነቱ … ቢያንስ ለኔ … የመጀመሪያ በሆነዉ ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ ተገኝቼ ገለፃ እንዳደርግ ለጋበዘኝ የቦስተን የቅንጅት ድጋፍ ኮሚቴ ያለኝን አክብሮትና ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

እዚህ ስብስባ ላይ ሁለት ኮፊያ ለማጥለቅ እገደዳለሁ፣ አንዱ የትብብሩ ሌላዉ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር፡፡ የግል አሰተያየቶቼም በየቦታዉ ብቅ-ብቅ ማለታቸዉ ስለማይቀር ከወዲሁ ላስገነዝብ እወዳለሁ፡፡

በተጨማሪም የመጣሁት ንግግር ለማድረግ ብቻ ሳይሆን ከናንተም ለመሰማትና ለመማር፣ ጥያቄአችሁንም በአግባቡ ለመመለስ ሰለሆነ መልእክቴ ግልጽና አጭር ይሆናል፡፡

ሕዝባችን መፈናፈኛ በሌለዉ የጭቆናና የአፈና ዓዘቅት ተዘፍቆ የሌት-ተቀን የመኖር ዋስትናው አጠያያቂ በሆነ ሁኔታ እንደሚገኝ ከማንም የተሠወረ አይደለም፡፡ ሕዝቡ ከዚህ መከራ ለመላቀቅ የሚያደርገዉ ትግል በተለያዩ ድርጅቶች ይመራል፡፡ ከነኚህ ለዉጥ-ፈላጊ ድርጅቶች የፖለቲካ ፕሮግራም በከፊል አለመጣጣም የተነሣ አንዱ ሌላዉን እንደ ትግል አጋሩ ሳይሆን እንደባላንጣዉ እንዲመለከትና በመካከላቸዉም ቀናና ገንቢ ግንኙነት እንዳይኖር ሆኗል፡፡ ከዚህም በላይ የየድርጅቶቹ ደጋፊዎች የጎሪጥ ከመተያየት አልፈዉ ለለዉጥ ስለማይተባበሩ የእስከዛሬዉ የተናጠል ትግል ከግብ አልደረሰም፡፡ ዲሞክራሲያዊ ስርአት እሰካሌለ ድረስ ልዩነቶችን በሕዝብ ድምፅ ለመፍታት ዕድል የለም፡፡ በተጨማሪም ከችግሮቹ ዉስብስብነትና የልዩነቶቸችን መካረር የተነሳ አንዱ ድርጅት የራሱን መፍትሔ በሌላዉ ላይ መጫን የማይችልበት፣ ቢችልም እንኳን ችግሩን ከማባባስ በስተቀር ብቻዉን ዘላቂ መፍትሔ ማስገኘት ቢያንስ አስቸጋሪ የሆነበት ታሪካዊ መስቀለኛ መንገድ ላይ ደርሰናል፡፡

ፓርቲዎች ህልማቸዉን እዉን ለማድረግ ሆነ ለታዩአቸዉ ችግሮች እልባት ለማስገኘት በነፃ ተንቀሳቅሰዉ አላማቸዉን የማሳካት ዕድላቸዉ ዝግ ነዉ ብንል ማጋነን አይሆንም፡፡ የፍትህና አስተዳደር ተቋሚት የገገርዉን ጥቅም ከማስጠበቅ የበለጠ ሚና የላቸዉም፡፡ በአፍሪካ የአለም-አቀፉ ማህበረሰብ የዲሞክራሲና ሰብአዊ መብት ፍቅር ከአፍ ልፈፋ አያልፍም፡፡ በጥቅሉ ሁላችንም ፍፁም አምባገነናዊ በሆነ ስርዓት ተተብትበን እንገኛለን፡፡ ካለዉ የከፋ የመብት ረገጣ፣ እየተባባሰ የመጣ ማህበራዊ ድቀትና አሳሳቢ የአከባቢ መራቆት የተነሳ የህዝቡ የግዜዉ ጥያቄና ፀሎት “እባካችሁ ተባበሩና ነፃ አዉጡኝ” ነዉ፡፡ የትብብሩን አመሠራረት ለመገምገም ሆነ ለመተቸት ጥያቄዎችን ከዚህ አሥቸጋሪ የጊዜዉ ሁኔታ ጋር ማገናዘብና አማራጩንም (ካለ ማለቴ ነዉ) በሚገባ ማሰላሰል ያስፈልጋል፡፡

እዚህ ላይ መጠየቅ ያለበት ለዉጥ ፈላጊዎች “የፕሮግራም ልዩነት አለን” በሚል መነታረኩና ተስማምተዉ ትግላቸዉን አለማቀናጀቱ የሚጠቅመዉ ማንን ነዉ የሚለዉ ነዉ? ተጎጂዎቹ በአምባገነን ሥረዓት ስር እየማቀቀ ያለዉ ሕዝባችንና ህዝቡን ከዚህ አስከፊ ህይወት

አዉጥተን ነፃነትና ዲሞክራሲን የሚያጎናፅፍ ሥርዓት እንገነባለን የሚሉ ድርጅቶች  ናቸዉ፡፡ ስለዚኽ የትብብሩ አለመፈጠር ሆነ መዳከም ብቸኛ ተጠቃሚ ወያኔና ወያኔ ብቻ እነደሆነ አያጠያይቅም፡፡ የትብብሩም ተቀዳሚ ተግባር የሕዝቡን የነፃነትና ዲሞክራሲ ትግል ከዚኽ ኣጣብቂኝ ማላቀቅ የሆነበት ዐብይ ምክንያት ይኸዉ ነዉ፡፡

ሁለተኛዉና ትልቁ ጥያቄ “ከዛ በኋላስ?” የሚለዉ ነዉ፡፡ እንደ ከዚህ በፊቱ አካሄዳችን መጨዉን የሚወሰነዉ ጉልበት፣ ብረትና ሸፍጥ ከኾነ ከገባንበት ኣዙሪት ከቶዉንም ልንላቀቅ ኣንችልም፡፡ ከፊታችን የተጋረጠዉ ጥያቄ “እንደ ከዚህ በፊቱ የለዉጥ ሂደቶች የአንዱ አምባገነን ማብቂያ የተተኪዉ ጉልበተኛ መብቀያ መሆን አለበት ወይ?” የሚለዉ ይሆናል ፡፡ ለዚህ ትብብሩ የሰጠዉ ምላሽ “መሆን የለበትም…በጭራሽ” ነዉ፡፡

የትብብሩ አላማ አሁን ተጠናዉተዉን ላሉት ችግሮች ብቻ መፍተሄ ማስገኘት ሣይሆን ለወደፊቱ የጋራ ሕይወታችንም የተሻለና ጠንካራ መሰረት መጣል ነዉ፡፡ አካሔዳችንም “የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነዉ” በሚለዉ ጠባብና ጊዜያዊ ግንዛቤ የሚመራ ሣይሆን እንዳለፈዉ ታሪካችን ኣንዱ ኣሸናፊ ሌላዉ ተሸናፊ የሚሆንበትን መንገድ ትተን ሁላችንም ኣሸናፊ የምንሆንበትን ዘላቂ የመፍተሄ ጎዳና መከተል ነዉ፡፡

ተከታዩ ጥያቄ “ዘላቂ መፍተሄ እንዴት ሊገኝ ይችላል?” የሚለዉ ይሆናል፡፡ ለዚህ የትብብሩ መልስ ሁሉን ያሳተፈ ኣገራዊ ጉባዔ ጠርቶ ችግሮቻችን ለአንዴና ለመጨረረሻ ጊዜ እልባት እንዲያገኙ፣ ይኸም በድርድር በስምምነትና በመቻቻል እነዲከናወን፣ እንዲሁም ከዚህ የሚመነጨዉ ሥርዓት ዲሞክራሲያዊና የግለሰቦችም ሆነ የቡድን ነፃነትን የሚያጎናፅፍ የሁሉም እዉቅና፣ ዉክልና፣ ተሳተፎና ነፃ ድጋፍ የገኘ እነዲሆን ነዉ፡፡

በ15 ዐመቱ ተሞክሮኣችን እንደተገነዘብነዉ ኣርቆ ማሰብ የተሳነዉ ወያኔ ይኸንን በፀጋ ይቀበላል ብሎ ማሰብ ኣይቻልም፡፡ ስለዚህ የትብብሩ የአጭር ጊዜ ተልዕኮ የወያኔን አምባገነን አገዛዝ በተባበረና በተቀናጀ ህዝባዊ ትግል ሁሉን-ኣቀፍ ጉባኤዉን እንዲቀበል ማሰገደድ፣ ካልተቻለ ደግሞ ከስልጣን ማስወገድ ይሆናል፡፡ ይህን እሙን ለማድረግ በሁሉም የስራ መስኮች ሠፊ መርሃ-ግብር ኣዉጥተን እየተንቀሳቀስን እንገኛለን፡፡

ባአንዳንድ የትብብሩ አባላት መካከል ያለዉ “የግለሰብ ወይስ የወል መብት ይቅደም?” የሚለዉ የአስተሳሰብ ልዩነት፣ ወደፊት በትግል እየተጣጣመና እየጠበበ ሊሄድ የሚችልና፣ የኣድልኦ አናሳ አገዛዝ በሰፈነበት ሁኔታ ፈፅሞ ሊያጣላን የማይገባና የማይችል ይመስለኛል፡፡ ሁለቱም መብቶች ክፉኛ ተረግጠዉ ባለበት ሁኔታ እንዲያዉም የቅንጦት እንዳይሆን እፈራለሁ፡፡ ከወል መብቶች ዋነኛዉ የብሄሮች መብትን የሚመለከተዉ ነዉ፡፡ የብሄሮች መብት ጉዳይ ለወያኔ ብቻ የተሰጠ ወይም የብሄር ኣርነት ድርጅቶች ብቻ ሊቆረቆሩለት የሚገባ ጥያቄ አይደለም፡፡ ህብረ-ብሄራዊ ፖለቲካን እናራምዳለን ብለዉ የተነሱ የኢትዮጵያ ድርጅቶች ባመዛኙ፣ ባለፉት 35 አመታት፣የብሄሮችን ጉዳይና የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብትን እንደ ዲሞክራሳዊና ሰብኣዊ መብት በመመልከት በየፕሮገራማቸዉ ያካተቱት ጉዳይ ነዉ፡፡ ከወያኔ ሥልጣን መቆናጠጥና የብሄር ጥያቄን ላእኩይ ተልዕኮ ማዋል ወዲህ ያጋጠመን ችግር ግን፣ የብሄሮችን ዲሞክራሳዊና የፍትህ ጥያቄ፣ ከወያኔ “የዘር” ኣድልኦ ጋር አንድ ኣድርጎ በመዉሰድ፣ወያኔ ለብሄር ጥያቄ ብቸኛ ተቆርቋሪ መስሎ በመስኩ እንድፈነጭበት መለቀቁ ነዉ፡፡ ከኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ጀምሮ ስንት መሰዋዕትነት የተከፈለበት ይህ የህዝቦች ጥያቄ፣ የወያኔ የግል አጀንዳ ተደርጎ፣ ለዘረኛና ጠባብ ፍላጎቱ መሆን የለበትም እላለሁ፡፡ ለዲሞክራሲና ሰብአዊ መብት የምንቆረቆር ሁሉ የራሳችን ኣድርገን ልንወስደዉ

ይገባል ባይ ነኝ፡፡ ይህ ቢሆን ለወደፊቱ አንድነታችን እዉነተኛና ታላቅ ገፀ-በረከት ለገስንለት ማለት ነዉ፡፡

በተጨማሪም ከኢትዮጵያ ህዝብ ወደ 70% የሚሆነዉ የኦሮሞና የአማራ ህዝቦች መሆናቸዉ ገሃድ የወጣ ሃቅ ነዉ፡፡ የወያኔ አናሳ አገዛዝ፣ ለኦሮሞዎች፣ ቅንጅት ያለፈዉን አስከፊ የጉልተኛ፣ የኢሰፓ ወይም የትምክህት አገዛዝን መልሶ ሊጭንብህ ነዉ ብሎ ያስፈራራል፡፡ ለአማሮች ደገሞ ኦነግ ሃገር ሊገነጥል ነዉ፣ አማሮችን ከኦሮሚያ ጠራርጎ ሊያስወጣ ነዉ የሚል ፕሮፓጋንዳ በመንፋት፣ ሁለቱን ታላላቅ ብሄሮች በማጋጨት ያለቀለተን የአናሳ አገዛዝ እድሜዉን ለማስቀጠል ሲራወጥ ይታያል፡፡

ትብብር ለነፃነትና ለዲሞክራሲ ይህን የወያኔ ዕኩይ የአናሳ ቡድን ተንኮል የምናመክንበትና፣ ሁለቱ ታላላቅ ብሄሮችም ሆኑ ሁሉም የሃገሪቱ ህዝቦች እርስ በርስ ከመጋጨት ይልቅ፣ በመከባበርና በመረዳዳት ከአናሳ አገዛዝ ነፃ ለማዉጣትና ለሁሉም ዘላቂ መፍትሄን በማስገኘት አዲስ የሰላምና የጋራ ብልፅግና ጎዳና ለመቀየስ የተቋቋመ ህብረት መሆኑንም በዚህ መድረክ ለማስመር እወዳለሁ፡፡

ህዝብን ከህዝብ ማጋጨት የወያኔ አይነተኛ የአገዛዝ ፊልስፍና ሆኗል፡፡ በዚህ በያዝነዉ በ1999 ዓም ብቻ እንኳን፣ የብሄር ግጭቶችን ለማድረግ የሚያስችለዉን ቀዳዳ በትብብሩ ስንደፍንበት፣ ሰሞኑን የሃይማኖት ግጭቶችን ወደመቀስቀስ ፊቱን ማዞሩ፣ በስልጣን ለመቀጠል የማይበጥሰዉ ቅጠልና የማይነቅለዉ ድንጋይ እንደሌለ ጉልህ ምስክር ነዉ፡፡ ሆኖም ይህንን የሃይማኖት ግጭት ለማምከንና ወደፊትም እንዳይነሳ ለመከላከል፣ ኦነግ ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበርና የትግል አድማሱንም በማስፋት እንቅስቃሴዉን እንደሚያጠናክር ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ፡፡

ስለትብብሩ ይኽንን ካልኩ ስለኦሮሞ ሕዝብ ጥያቄና ስለ ኦነግ አንድ ሁለት ብዬ የማጠቃለያ መልእክት በማሰተላለፍ ገለፃዬን አበቃለሁ፡፡

የኦሮሞ ሕዝብ ጥያቄ ሁለት መሠረታዊ ምንጮች አሉት፡፡ አንደኛዉ እስከዛሬ የዘለቀ መራር የጭቆናና የብዝበዛ ታሪክ ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ እንደማንኛዉም ብሔር ህዝቡ እራሱን በራሱ በነፃ የማስተዳደር፣ ቋንቋዉን ባህሉን የመጠቀም የማሳደግ፣ ብሄራዊ ማንነቱን የማስጠበቅ፣ በንብረቱና በሕይወቱ እንዲሁም በወደፊቱ ኑሮዉ ላይ ሙሉ የማዘዝና የመወሰን መብት መነፈጉ ነዉ፡፡ ይኽ የዴሞክራሲና የሠብአዊ መብት ጥያቄ ደግሞ የኦሮሞ ብቻ ሣይሆን ሌሎችም የሚጋሩት ነዉ፡፡

የኦሮሞ ሕዝብ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ ቀንድም ብዙ ከሚባሉት አንዱና ምናልባትም በሁለንተናዊ መልኩ የአከባቢዉም እምብርት በመሆኑ በኢትዮጵያ ለነፃነትና ዲሞክራሲ በሚደረገዉ ትግል ትልቅ ሀላፊነት እንዳለበት ይገነዘባል፡፡ ኦነግ ለትብብሩ መመስረት የወሰደዉ ጉልኽ አስተዋፅዖ ይኽንን ሀላፊነት ከማገናዘብ የተነሣ ነዉ፡፡

የኦሮሞ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ባህል በታሪክ የሚዘከር ኽያዉ የማንነቱ መገለጫ ብቻ ሣይሆን አሁንም ሊዳብር የሚችልና ወደፊት ሁላችንም ለምንመኘዉ የዲሞክራሲ ሥርዓት መሠረት የሚሆን ነዉ፡፡ ከዚህም በላይ የህግ የበላይነት፣ የመቻቻል፣ ቂምና ጠብን ሣይሆን እርቅንና ቅንነትን መሠረቱ ያደረገ የፖለቲካ ባህል፣ በኦሮሞ ስነልቦና ዉስጥ ሥር የሰደዱና በባህሉም ትልቅ ቦታ ያላቸዉ ፅንሰ-ሃሳቦች ናቸዉ፡፡ የህግ የበላይነት የሰፈነበት ነፃና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ለኦሮሞ ሕዝብ ብቻ ሣይሆን ለሁሉም ሕዝቦች ሠላም ብልፅግናና እድገት የሚበጅ

በመሆኑ ኦነግ በፍቃደኝነትና በጋራ ጠቀሜታ ላይ የተመሰረተ አንድነትን እንደሚሻ፣ ለዚህም እዉን መሆን ኣጥብቆ እንደሚታገል ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ፡፡
ይህንን ካልኩ በኋላ ሦስት የማጠቃለያ ሀሳቦችን በማቅረብ ንግግሬን እቋጫለሁ፡፡

1) በሙዚቃ ትዝታን የምናዘወትረዉን ያኽል የፖለቲካ ዉይይቶቻችን በኣመዛኙ በታሪክ ትንታኔ ተጀምረዉ የሚያልቁ ይመስላሉ፡፡ ከዚኽ ባሕርይ የተነሣ የፖለቲካ አቋሞቻችንም በታሪክ አፈታትና ምንነት እነዲሁም ላለፉት ክንዋኔዎች በምንሰጠዉ ትንተና ይለያይ ይሆናል፡፡ በታሪካችን ለነበሩ ግለሰቦች የምንሰጠዉም ምንነትና ቦታ ኣንዳንዴ ሆድና ጀርባ ሊሆን ይችላል፡፡ በሕዝብ ወሳኝነት እስከተግባባን ድረሥ ይኽ መሆኑ ስለወደፊቱ ኣንድ ህልም ከማለም ሊያግደን ኣይገባም እላለሁ፡፡ የምንኖረዉና የምናልመዉ ስለወደፊቱ እንጂ ስላለፈዉ ስላልሆነ ያለፈዉ ታሪካችን ቢያስማማንም ባያስማማንም ዛሬ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ አብረን ለመክፈት የሚያግደን አንዳችም ምክንያት ሊኖር አይገባም፡፡ ይኽን ስል ያለፈዉን የግፍና የመከራ ታሪክ እንርሣ ማለቴ ኣይደለም ፡፡ የምለዉ ሁላችንም ከበጎ ይሁን ከመጥፎ የታሪካችን ገፅታዎች ተምረን የታሪክ እስረኞች ሳንሆን አሁን ያለንበትን ችግር በጋራ ለመወጣትና የወደፊቱ የህዝቦቻችን ግንኙነት በመከባበርና በመፈቃቀድ ላይ እንዲመሰረትና እንዲጎለብት አብረን እንስራ እላለሁ፡፡

2) ህላችንም "የኛ" የምንለዉ ሕዝብ በአስከፊ ህይወት ዉስጥ እንደሚገኝ ከሁላችሁም የተሠወረ ኣይደለም፡፡ አብዛኞቹ ችግሮቻችን ተለያይተን ቀርቶ በጋራ ብንረባረብባቸዉ እንኳን በቀላሉ ለመፍታትም ሆነ ለጊዜዉ ለመቅረፍ የሚያስቸግሩ ናቸዉ፡፡ ለአሁኑም ሆነ ለወደፊቱ የሚያዋጣን ከሚለያዩን ይልቅ በሚያቀራርቡን ላይ ማተኮር ስለሆነ ትብብሩ በዘረጋዉ የጋራ የትግል መድረክ በመተማመን ወደፊት እንጓዝ እላለሁ፡፡ ከሁሉም ወገን የፍርሃትና ጥርጣሬ ስሜት እንዳለ ግልፅ ነዉ፡፡ በጋራ የምንታገልበት ሂደት፣ ይበልጥ ለመተዋወቅ ዕድል ስለምናገኝ፣ ኣንዳችን በሌላችን ላይ መተማመን እየፈጠርን የምንሄድበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ ይህ ኣንዳችን የሌላችንን መከፋት፣ ብሶትና ፍርሃት መረዳት የምንችልበትን ዕድል ይፈጥራል፡፡ ይህ ከሆነ የጀመርነዉ የጋራ ጉዞአችን ረዥምና ዘላቂ ይሆናል፡፡

3) ትብብር ለነፃነትና ለዲሞክራሲ የሕዝባችን የረዥም ግዜ ምሬትና የመፍትሄ ጥማት የወለደዉና ጊዜዉ የደረሰ ሃሳብ ስለሆነ ከግብ እንዳይደርስ የሚያስቀረዉ ምድራዊ ሃይል ኣይኖርም፡፡ የተቀደሠ መንገድ በመሆኑም ከብዙ አቅጣጫዎች አያሌ መሰናክሎች እንደሚጠብቁን ኣውቀን መንቀሣቀስ ይኖርብናል፡፡ መቼም የወደፊቱን መተለም ያስቸግራል፡፡ ነገር ግን ኣንዳንዶች እንደሚሉን አብሮ መሥራቱ የመበታተንን አደጋን እዉን የሚያደርግ ሣይሆን መተማመን እንዲጎለብትና አዳዲስ የኣንድነት ዲልድዮች እንዲገነቡ የሚረዳ እንደሆነ ከወዲሁ መተለም አያዳግትም፡፡ ትብብሩ የተመሠረተበት ምሰሶዎች ጠንካራ ምክንያታዊ መሰረቶች ያሉት ቢሆንም ዉሳኔዉን መዉሰዱ ወኔ የሚጠይቅ ነበር፡፡ አሁንም በሂደት ሊያጋጥሙን የሚችሉ ችግሮችና እንቅፋቶች መቋቋም ትልቅ ወኔ ይጠይቃል፡፡ የትብብሩ መፈጠር ብቻ ካሁኑኑ ለወያኔ የጎን ዉጋት ሆኗል፡፡ የሁላችንና የእያንዳንዳችን ሙሉ ድጋፍና ተሳትፎ ከታከለበት ትብብሩና መላዉ ህዝባችን በአጭር ጊዜ ዉስጥ ድልን ይቀዳጃል፡፡ ይኽን ከደረግንና የትላንቱ ሣይሆን የነገዉ ሠዎች ሆነን ከተገኘን የመከራና የሃዘን ኑሮአችን ወደ ዘለቄታዊ ደስታና ብሩህ ተስፋ የተሞላበት ህይወት እንደሚለወጥ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ ይህን በህይወት ማየት የሁላችንም ምኞትና ተስፋ ነዉ፡፡

ስላአዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ፡፡